ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

የእኛ መዝገቦች እንደሚያሳዩት ልጅዎ **measles, mumps, and rubella** (**MMR፣ ከኩፍኝ፣ ጆሮ ደግፍ እና ሩቤላ) ክትባት ነፃ መሆኑን የሚያሳይ Certificate of Exemption (ነፃ የመሆን የምስክር ወረቀት) በፋይል ላይ አለው።**

በፕሮግራማችን ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ **የኩፍኝ ወረርሽኝ** ከተከሰተ፣ የኩፍኝ በሽታ የመከላከል አቅም (መከላከያ) ማረጋገጫ ማቅረብ የማይችል ማንኛውንም ሰው ለበሽታው ከተጋለጠበት የመጨረሻ ጊዜ ጀምሮ **እስከ 21 ቀናት ድረስ ቤት ውስጥ እንዲቆይ** የጤና ጥበቃ መምሪያ ሊያስገድድ ይችላል። ይህም የኩፍኝ በሽታ ስርጭትን ለማስቆም ይረዳል።

ኩፍኝ በጣም ተላላፊ ነው እንዲሁም በፍጥነት ሊሰራጭ ይችላል። በተጨማሪም ከባድ የጤና ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ እባክዎን የWashington State Department of Health (የዋሽንግተን ስቴት የጤና መምሪያን) ይጎብኙ፡- doh.wa.gov/measles።

ስለ ኩፍኝ በሽታ እና ስለ MMR ክትባት ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ከጤና እንክብካቤ ባለሙያዎ ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታዎታለን።

ከሰላምታ ጋር፣